**ክፍል 1**

## የአማራን ማንነት በአማራ ድርጅት

አማራ በኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ያላንዳች ማወላወልና ማመንታት በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው።
ሩቅ ሳንሄድ ወያኔ ከገባበት ከግንቦት ወር 1983 ዓም ጀምሮ እንኳን ብንመለከት፣ ሁሉም ነገዶች የጎሳ ድርጅቶች አቋቁመው የኢትዮጵያን አንድነት በናደው በሽግግር መንግሥት ተብየው ተወክለው ሲካፈሉ፣ አማራው ጎሳን ባለማቀንቀኑና በኢትዮጵያ አንድነት ፀንቶ በመቆሙ ያልተካፈለ ብቸኛው ህዝብ ነው።

### <u>የትግሬ ዘረኞች በአማራው ላይ እንዴትና ለምን ዘመቱበት?</u>

የትግሬ ጠላት አማራ እንደሆነ አበክረው እየነገሩን፣እኛ አማሮች ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ያልናቸው፣ የትግሬ ወራሪዎች ! አመጣጣቸው፣ (1ኛ)"አማራን አጥፋ፣ትግሬን አፋፋ" (2ኛ)" ትግሬን አልማ፣ሌላውን አድማ" (3ኛ) "ትግሬን አደልብ፣ ሌላውን እለብ" ሥለሆነ፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊና ሕዝባዊ አንድነት በጎሳ በመበታተን ኃይላቸውን አጠናከረው፣አማራው የሚኖርባቸውን ለምለም ቦታዎች አሥለቅቀው ትግሬዎችን ተጠቃሚ በማድረግ የትግሬን ሕዝብ ድጋፍ ማሰባሰብና እሥከቻሉም ድረስ እየመዘበሩ መኖር ነው።

ይህ መሠሪ ሥራቸው ከታወቀባቸውና ጥያቄ ካስነሳ ደግሞ (አሁን እንደሚያደርጉት ማለት ነው) እሥከቻሉ ድረስ የአማራን ሕዝብ ከማጥፋት አይመለሱም።
ይህን ሁሉ አድርገውም አቅም ቢያንሳቸውና የማይችሉ መሥሎ ከታያቸው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር ጠራርገው በመውሰድና ትግሬዎችንም እሥከማስወጣት ይደርሳሉ።

ይህንን ሁሉ ለማድረግ ሁኔታው ቢቀድማቸው ደግሞ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የበተኗቸውን ትግሬዎች ጥለው፣ራሳቸው በነፍስ አውጭ ፍርጠጣ ታግዘው ትግራይ ትግሪኚን መሥርተው ለመኖር ነው። ዛሬም ተግባራዊ ለማድረግ የጀመሩት ይህንኑ ሀቅ ነው። ጥያቄው ግን ሌሎቻችንን ሲያምሱና ሲቆሉ ኑረው፣ወደትግሬ ኮብልለው በሠላም ለመኖር እንደሚችሉ እንዴት እርግጠኛ ሊሆኑ ቻሉ ነው።

እነኚህ የትግሬ ወራሪዎች! ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት በአገሪቱ ውስጥ ለደረሱት ሁሉ ችግሮች በዳይና ጨቋኝ፣"የኢትዮጵያ ሀገራዊና ህዝባዊ አንድነት በሚል የቆሙትና የብሔሮችን እኩልነት የማይቀበሉት ትምክህተኛ አማሮች ናቸው" ብሎ በመስበክ፣የተለያዩትን ጎሳዎች በየነገዳቸው አደራጅቶ፣የዝመቱባቸው ቅስቀሳ በማካሄድ ነው ብለው በማመን ነው።
ሥለሆነም ትግሬዎች በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በአነግ ተባባሪነት፣ከተገንጣዮችና ከጎሳ አቀንቃኞች ጋር እጅና ጓንት በመሆን በመሳሪያ ኃይል ታጅበው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የአማራውን ህልውና ለማጥፋት ዘመቱ።

በዚህም መሠረት የአማራውን ታሪካዊ ቅርስ በመዝረፍና በማራቆት፣በኢኮኖሚውም እንዳያድግ የኢኮኖሚ አፈና በማድረግ፣ባህሉን በማንቋሸሽና በማራከስ፣ ዘሩ ቀጣይነት እንዳይኖረው መካን በማድረግ፣ በራሱ ላይ እምነት አጥቶ በማንነቱ እንዲያፍር፣ ሞራሉን በመንካትና ቅስሙን በመሥበር፣ ሥር ነቀል የሆነ የሥነ ልቦና ጦርነት ያለማቋረጥ ለ25 ዓመታት እንዲካሄድበትና ሰቆቃውም ሥር እንዲሰድ አደረጉ።

እነኚህ የትግሬ ወራሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ በአገራችን በኢትዮጵያ የሚታየው ከቡሃ ላይ ቆረቆር እንዲሉ፣ ከርሀብና ከቸነፈር በባሰ መልኩ ዘረኝነት ጣሪያ ነክቶ ነው።

### <u>አማራው ህልውናውን ለማስጠበቅ ምን እያደረገ ነው?</u>

ይህ ሁሉ ሲሆን አማራው ያንን የተለመደ ትዕግሥቱንና ሆደሰፊነቱን መሳሪያ በማድረግ የጎሳውን ጥቅምና ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነትና ከሌሎች የኢትዮጵያ ጎሳዎች አብልጦ ባለማየቱ በዘር መደራጀት ከሰማይ የራቀ ሀሳብ ሆኖበት ቆይቶ ነበር።
ነገር ግን አማራው ከየትኛውም አቅጣጫ እየተዋከበና ግፉ እየተበራከተ በመጣበት ወቅት፣ይህንን የመሰደድና የግፍ ብሎም የሞት ፅዋ ተጎንጭቶ፣ማንነቱና ህልውናው እያሽቆለቆለ ሲሄድና አደጋ ላይ ሲወድቅ፣

ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመምከር በ1984ዓ.ም የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅትን (መዐሕድን) አቋቁመው ችግሩን ለመቅረፍ በጣሩበት ወቅት የትግሬ ወራሪ፣ፕሮፌሰርን ከመሰሎቻቸው ጋር ለእሥር ዳርጎ ለሞት ሲያበቃቸው ድርጅቱም ተዳከመ።

አማራው ከሚደርስብኝ ግፍ ምናልባት የኢትዮጵያ አንድነት ያድነኝ ይሆናል ብሎ በማሰብ በመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ጥላ ሥር ቆመ።

የቅንጅትም ትልቁ ድርጅት በመሆን ቢነሳም ቅንጅት ፈረሰ፣ የአንድነቱ ድርጅት በሰላም ትግል ሥም ቢቀጥልም፣ የአማራውን መገደል አልገታውም፣ አላስቆመውም።

እንደውም ከድሮው ባልተናነሰ መልኩ እየጨመረ ሄደ። በመሆኑም እሥከአለፈው ዓመት ድረስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር አማራ ተገሏል፣ታሥሯል ብሎም የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ጠፍቷል፣ማለትም ከአምሥት(5) ሚሊዮን  በላይ ጠፍቷል።

ለግንዛቤ ያህል! መዐሕድን ወደመኢአድ ከመቀየር ይልቅ ወደሁለገብ ትግል ቀይረን እያጠናከርን ብንቀጥል ኖሮ እስካሁን ድረስ ያላንዳች ጥርጥር በአሸናፊነት እንቋጨው ነበር እላለሁ።

የትግሬ ወራሪዎች ይህን ሕዝብ በቀንደኛ ጠላትነት ፈርጀው፣አገርና ሠው አልባ ለማድረግ ቆርጠው ሥለተነሱበት ሕዝቡን ከመጨረስም ባሻገር ግዛቶችንም ተቀራመቷቸው።ከጎንደር የተቀሙት፣ እነ ወልቃይት፣ጠገዴ፣ሁመራ፣ጠለምት፣ ወዘተ ሲሆኑ፣ከወሎ ደግሞ እነራያ፣ዋጃ፣ኮረም፣አላማጣ፣ አበርገሌ፣ወዘተረፈ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ከሞት የተረፈው ሕዝብም "አማራ እንጅ ትግሬ ሥላልሆን ወደአማራ ክልል እንመለስ" በሚል ጥያቄውን ለብዙ አመታት ቢያቀርብም ትግሬዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው የአገሬውን ሕዝብ እየገደሉና እያባረሩ ትግሬዎችን ብቻ ማሥፈር ቀጠሉበት።

ይህ ማብቂያ የሌለው ግድያ እየባሰ በመሄዱ አማራው እንደገና የአማራ ድርጅት ፈጥሮ የአማራ መብት ይጠበቅ በማለት ሕዝብን እያነቃ ባለበት ወቅት፣በተለይ ደግሞ ብዙ ዓመታትን ያሥቆጠረው በወልቃይት ኮሚቴ አማካይነት እየተገፋ የመጣው የወልቃይት የአማራ ማንነት ጥያቄ፣ ፈንቅሎ መውጣት፣ በአማራነት ተደራጅቶ መመከትም እንደሚቻል ለሁላችንም ትምህርትና ድፍረት ሰጥቷል።

ዛሬ እንዳየነው በ25ዓመት የኢትዮጵያ አንድነት ትግል ያላሥመዘገበውን ውጤት፣ በአማራ አንድነት ትግል የአማራ ማንነት ጥያቄ ጎንደር ላይ አሥመስክሯል።

የትግሬ ዘረኞች! የአማራ ዘር ዳግመኛ እንዳይነሳ አድርገን አከርካሪውን ሰብረነዋል፣ የኦርቶዶክስ ዕምነትም ከአማራው ጋር አልቆለታል ብለው በእርግጠኝነት ተናግረው ሳይጨርሱ፥የአማራው ወጣት በአርንጓዴ ቢጫ ቀይ ሠንደቅዓላማ ታጅቦ የአማራን ማንነት ጥያቄ ይዞ ብቅ ሲልና ከኦሮሞው ጋር ሲናበብ ወያኔዎች የሚይዙትንና የሚጨብጡትን እንዳጡ ታዝበናል።

ይኸውና ከሐምሌ 5ቀን 2008ዓም ጀምሮ ደግሞ የትግሬ አጋዚያን ወራሪዎች  ለይሥሙላ ባስቀመጡት ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብየው የወላይታ ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ ተላላኪነት በአማራው ላይ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንዲታወጅበት ሆኗል።ከዚህ ቀን ጀምሮ ጎንደርና ጎጃም የጦር ቀጠና ሆነዋል።ልጅ አዋቂ ሳይለዩ እየገደሉት እንደሆነ ይታወቃል።

እነኚህ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከትግሬ ወራሪዎችና ባንዳዎች ጋር ግብ ግብ ገጥመው አጥንታቸውን ደማቸውንና ህይወታቸውን እየሰጡ ለነፃነታቸው መሥዋዕት የሆኑትና የሚሆኑት ለአማራ የማንነት ጥያቄ መልስ ለማሥገኘት ነው።

ይህን ትግል የለኮሰውና ያቀጣጠለው አብዛኛው ወጣት፣ወያኔዎች ሲገቡ ከ15ዓመት በታች የነበረና ወያኔ ከገባ በኋላ የተወለደ ነው ማለት ይቻላል።በመጀመሪያው የወያኔ ግድያ በባህር ዳርና በተወሰኑ አካባቢዎች በጀግንነት ከወደቁት 49ኙ ውስጥ ብዙሀኑ ከ40ዓመት በታች ናቸው።

ይህን ካልኩ በኋላ በሸዋ ማጀቴና በወሎ መቄት ከተደረጉት እንቅስቃሴዎች ውጭ በዚያ አካባቢ በሥፋት እንቅስቃሴ ሲካሄድ አይደመጥም።በአዲስ አበባማ ከእነአካቴውም የለም ማለት ይቻላል።የወያኔ ግብፃዊ፣ ሻቢያዊ እና አሸባሪያዊ የበሬ ወለደ የውሸት ፕሮፓጋንዳ አማራውን ሲያልፍ እንደማይነካው ዕምነቴ ነው።

ሥለሆነም አማራነት! ከሸዌነት፣ከጎንደሬነት፣ከጎጃሜነት እና ከወሎዬነት በላይ እንደሆነ ተረድተህ፣ የሸዋም የወሎም የአዲስ አበባም በጠቅላላው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የምትኖር አማራ አንገትክን ቀና አድርገህ ተሰባስበህና ታጥቀህ "ሊገል የመጣን ጌታዬ፣ጌታዬ ቢሉት" መግደሉን ሥለማይተው፣ "ሳይቃጠል በቅጠል ብለህ" ቀኑ ሳይመሽ፣በአማራነትህ ከጎንደርና ከጎጃም አማራ ወንድምህና እህትህ ጎን ቁም።

ቀጥሎም ዘርህን ለማጥፋት ጦር ያወጀብህን ከውጭ ጠላት የማይለየውን፣የትግሬ ዘረኛ ቡድን አውድም።ይህን ሳታደርግ ከቀረህ ዛሬ በጎንደርና በጎጃም የሚደረገው፣ ነገ በአንተ ላይ እንደሚፈፀም በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ሥለዚህ ዛሬ የአማራው ሕዝብ መሠረታዊና ወሳኝ ጥያቄ! የአማራ ማንነት ጥያቄ በመሆኑ፣ ይህም አሸናፊ ሆኖ የሚወጣውና ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፣

(1ኛ)የኢትዮጵያ አንድነት በሚሉ ወገኖች ሳይሆን በቅድሚያ የአማራን ዘር በአንድነት ሰባስቦ ሊያታግልና ሊታገል የሚችል ኢትዮጵያ ውስጥ በራሱ ወገኖች በተቋቋመ ጠንካራ የአማራ አንድነት ድርጅት ተመርቶ ግቡን ሲመታ እና
(2ኛ) ለትግሬ ዕብሪተኞች በሚገባቸው ቋንቋ መልስ መሥጠት ሲቻል ብቻ ነው።ዘረኞችና ከፋፋዮች ልካቸውን እሥካላወቁ ድረስ የአማራው ሕዝብ በሠላም አይኖርም።

የዚህ ድምር ውጤት የራሱን መብት፣ማንነቱንና ህልውናውን አሥከብሮ፣በህይወት ለመኖር አሥተማማኝ ዋስትና ያጎናፅፈዋል። አማራው ከምድረገፅ ከጠፋ ደግሞ የኢትዮጵያ አንድነትም አይታሰብም።

ይቀጥላል